የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

## የኮሮና ቫይረስ በሽታ ምላሽ አሰጣጥን (የኮቪድ-19) አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው ተጨማሪ 247 የላብራቶሪ ምርመራ ሶስት (3) ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በሀገራችን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሰባ አራት (74) ደርሷል፡፡ በሌላ መልኩ በትላንትናው ዕለት አራት (4) ሰዎች ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ በሀገራችን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር አስራ አራት (14) ደርሷል፡፡ በዛሬው ዕለት በቫይረሱ የተያዙ ታማሚዎች ዝርዝር ሁኔታቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፣

| ተ.ቁ | ዜግነት | የመኖሪያ ቦታ | እድሜ | ፆታ | የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ | በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | 40 | ወንድ | የለውም | የለውም |
| 2 | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | 23 | ሴት | የላትም | አላት |
| 3 | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | 72 | ወንድ | የላቸውም | የላቸውም |

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 4110 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 247 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 3 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 55 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 0 |
| በዛሬው ዕለት ያገገሙ | 4 |
| ጠቅላላ ያገገሙ | 14 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 3 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 74 |

ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት፡
በመጪው ጥቂት ቀናት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረውን የትንሳኤ በዓልን አስመልክቶ የሚከናወኑ የበዓል ግብይቶች በጥንቃቄና አካላዊ ርቀትን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን እናስገነዝባለን፡፡
በተጨማሪም በበአል ወቅት በቤተሰብና በጎረቤት መሃከል የሚካሄዱ በአካል ከመጠያየቅ እንድንቆጠብ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡ ይሁንና በበዓላት ወቅትም የጤና ተቋሞቻችን ለዚሁ ጉዳይ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑ ታውቆ በማንኛውም ሰዓት በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እናሳስባለን፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796

በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ማግኘት ይቻላል፡

ዶ/ር ሊያ ታደሰ

የጤና ሚኒስትር

ሚያዝያ 5 ፣ 2012 ዓ.ም